የሠ/መ/ቁጥር 203965
ጥር 27 ቀን 2014 ዓ/ም

**ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ**

**ተሾመ ሽፈራዉ**

**ሀብታሙ እርቅይሁን**

**ብርሃኑ መንግሥቱ**

**ነጻነት ተገኝ**

**አመልካች፡- እድሉ አያል**
**ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ አ.ማ አልቀረቡም**

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ የሥራ ክርክርን የሚመለከት ነዉ፡፡አመልካች በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል በአንፊሎ ወረዳ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ ተጠሪ በቋሚነት ቀጥሮኝ ለ17 ዓመታት በተለያዩ የሥራ መደቦች ላይ ስሰራ ቆይቼ በሥራ ላይ ቋሚ የአካል ጉዳት ስለደረሰብኝ ብቻ ያለማስጠንቀቂያ እ.ኤ.አ በቀን 18/05/2019ዓ/ም ከሕግ አግባብ ዉጭ አሰናብቶኛል፡፡ዉሉ በተቋረጠበት ጊዜ ደመወዜ ብር 8482.00 ነበር ፡፡ስለሆነም ስንብቱ ሕገ ወጥ ነዉ ተብሎ ለ2 ዓመት በበዓላት ቀናት የሰራሁበትን በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 75/1 መሰረት ብር 17940.00፣የ313 ቀን የዓመት እረፍት ብር 172,776.00፣የእሁድ እረፍት ቀን ለ2 ዓመት ያሰራኝን ብር 52,992.00፣ለ2ዓመት ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ዉጭ ለ600 ቀናት በቀን ለ4 ሠዓት የሰራሁበትን ብር 103,500.00፣በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀት 43/4 መሰረት የ6 ወር ደመወዝ ብር 50,892.00፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የ2ወር ብር ብር 16,964.00፣በአዋጁ አንቀጽ 40/3 መሰረት የ2ወር ደመወዝ ብር 16,964.00፣ለ17 ዓመት አገልግሎት በአዋጁ አንቀጽ 40/1 መሰረት ብር 53,719.33፣በአዋጁ አንቀጽ 109 መሰረት የአካል ጉዳት ካሳ ብር 508,920.00 እንዲከፍለኝ፣ክፍያ በ7 ቀን ዉስጥ ሳይከፈል ለዘገየበት 3 ወር ደመወዝ ብር 25,446.00፣በተለያዩ ቅርንጫፎች ስሰራ ከደመወዘ 20% የተጠራቀመ የቁጠባ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ገንዘብ ብር 150,205.17 እና ለ17 ዓመት ከደመወዜ የቆጠብኩትን ብር 346,065.60 በአጠቃላይ ተጠሪ ወሌን ከሕግ ዉጭ ስላቋረጠ ብር 959,042.93 እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

ተጠሪ ለክሱ በሰጠዉ መልስ አመልካች ከሥራ እስከተሰናቡቱበት ቀን 10/09/2011ዓ/ም ድረስ በተጠሪ ዳሌ ላሎ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሠራተኛ በመሆን ሲሰራ ቆይተዋል፡፡የወር ደመወዝ ብር 8482.00 ሲከፈላቸዉ ነበር። በሥራ ላይ እያሉ ቋሚ የአካል ጉዳት የደረሰባቸዉ መሆኑ እዉነት ነዉ፡፡ነገር ግን አመልካች ከተጠሪ ብድር አሰጣጥና አመላለስ አሠራር ዉጭ ተበዳሪዎች ሙሉ አመለት በተበደሩት ገንዘብ ሰርተዉ እንዲመልሱ ከሚደረገዉ አሰራር ዉጭ በ2016 እና 2017 ለተበዳሪዎች በአንድ ቀን ገቢ አድርጎ በሁለተኛ ቀን ለሌላ ተበዳሪ ተመልሶ እንዲሰጥ ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡በዚህ መሰረት ተበዳሪ ከሚበደረዉ ብድር 10% እና 5% ትርፍ የሚያገኙ ተበዳሪዎች እንደነበሩ ተደርሶባቸዋል።በዚህ አግባብ ተጠሪ ሲሰሩ ከነበሩበት ከሁለት አመት በፊት ሲሰሩ በነበረዉ ቅርንጫፍ ደንበኞቻችን ከድርጅቱ የህብረተሰቡን ኑሮ ለማሻሻል ከያዘዉ ራዕይ የሚቃረን በመሆኑ በፈጸሙት ያልተገባ ጥቅም የማግኘትና የማታለል ተግባር ስለመፈጸሙ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(1/ሐ እና መ) መሰረት በሕጋዊ መንገድ ተሰናብተዋል፡፡አመልካች በአንቀጽ 27/1 መሰረት ስለተሰናበቱ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ አይገባቸዉም።በሕግ አግባብ ስለተሰናበቱ የስንብት ክፍያ እና ካሳም ሊከፈላቸዉ አይገባም።አመልካች የሚሰሩበት ሥራ ትርፍ ሰዓት የሚያሰራ ባለመሆኑ ከዚህ አንጻር ትርፍ ሰዓት ፣ በእረፍትና በበዓላት ቀናት ሠርቻለሁ በማለት እንዲከፈላቸዉ የጠየቁት ሊከፈላቸዉ አይገባም፡፡ የ17 ዓመት የአገልግሎት ክፍያ ብለዉ የጠየቁት ብር 53,719.33 በአዋጁ አንቀጽ 39/ለ መሰረት በድርጅቱ አሰራር መሰረት ስለፈጸም ጥቂዉ ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡የአካል ጉዳት ካሳ በተመለከተ በሆስፒታል ቦርድ የተወሰነ ማስረጃ አላቀረቡም።20% የቆጠብኩት ይመለስልኝ በማለት የጠየቁት አይነት ቁጠባ በድርጅቱ የለም፡፡ የፕሮቪደንት ፈንድ በተመለከተ ከድርጅቱ የተበደሩትን ገንዘብ ከፍለዉ ይህንን የሚያሳይ ማስረጃ ሲያመጡ ይከፈላቸዋል፡፡ያለማስጠንቀቂያ ተሰናበትኩኝ የሚሉትን በተመለከተ ከዚህ በፊት እ.ኤ.አ በቀን 30/12/2015 የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ስለተሰጣቸዉ ያለማስጠንቀቂያ ተሰናበትኩኝ የሚሉት ሀሰት ነዉ፡፡

ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 20357 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 15/07/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ የአመልካችን የስራ ዉል ያቋረጠዉ ከድርጅቱ አሠራር ዉጭ ያለደብዳቤ ሌላ ቦታ ሄደዉ በመስራት የድርጅቱን ተአማንነት ዝቅ የሚደርግ ተግባር በመፈጸሙ ስለሆነና ይህም ደርጊታቸዉ ድርጅቱ እ.ኤ.አ ሚያዚያ 2018 ባወጣዉ ደንብ አንቀጽ 9.2.1(ቀ እና ሠ)፣3.3፣3.9.9 እና 3.9.10 መሰረት ከሥራ የሚያሰናብት በመሆኑ ሥንብቱ ሕጋዊ ነዉ፡፡ስለሆነም አመልካች ያልተጠቀሙበትን የ2011 የዓመት እረፍት ብር 9047.46፣ የፕሮቪደንት ፈንድ ብር 105,205.17፣ 20% ቋሚ የአካል ጉዳት እንደደረሰባቸዉ ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የመጣዉ ማስረጃ ስለሚያሳይ የአካል ጉዳት በደረሰባቸዉ ጊዜ ሲከፈላቸዉ የነበረዉ ደመወዝ ብር 4306.00 እንደሆነ ስለተረጋገጠ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 109(4/ለ) መሰረት በ5 ዓመት ተባዝቶ ካሳ ብር 51,672.00 በድምሩ ብር 165,924.63 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፈላቸዉ ወስኗል፡፡

አመልካች በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለቀለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 29410 ላይ በቀን 13/09/2012ዓ/ም በሰጠዉ ብይን ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መሰረት ሰርዞባቸዋል፡፡በመቀጠል አመልካች አቤቱታቸዉን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዉ ችሎቱ በመ/ቁጥር 333150 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 06/04/2013ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች በቀን 06/07/2013ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪ የስራ ዉሌን ያቋረጠዉ በ2016 እና በ2017ዓ/ም ተፈጸመ የተባለዉን ጥፋት መሰረት በማድረግ ሆኖ ሳለ የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ስንብቱን በአዋጁ አንቀጽ 27/3 ስር የተደነገገዉ የ30 ቀን ካለፈ በኋላ መሆኑን እያወቀ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረብኩትን ክርክር አልፎ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ተጠሪ የአመልካች ወርሃዊ ደመወዝ ብር 8482.00 እንደነበረ ሳይክድ የስር ፍርድ ቤት ለተጠሪ የአካል ጉዳት ካሳ ሲወስን የወር ደመወዜን በብር 4306.00 ሂሳብ አስልቶ የወሰነዉ በአዋጁ አንቀጽ 109 እና በሰ/መ/ቁጥር 49273(ቅጽ 9) ላይ የተሰጠ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሊታረም የሚገባዉ ስህተት ነዉ፡፡የአመት እረፍት አዘግይቶ በመክፈሉ ቅጣት ሳይወሰን መታለፉ፣የአመት እረፍት ከጠየቅሁት ተቀንሶ መወሰኑ እና ሌሎች ክፍያዎች በተየቅሁት መሰረት ያልተወሰነልኝ አለአግባብ ስለሆነ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ አመልካች ሊከፈላቸዉ የሚገባዉ የጉዳት ካሳ ሊሰላ የሚገባዉ በአመልካች ላይ ጉዳት በደረሰበት ጊዜ ሲከፈላቸዉ በነበረ ደመወዝ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 109 አንጻር ተጠሪ ባለበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 16/02/2014ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ይዘቱም በአጭሩ አመልካች የጉዳት ካሳ እንዲከፈላቸዉ ክስ ያቀረቡት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/1 ስር የተደነገገዉ የ2 ዓመት ጊዜ ካለፈ በኋላ ነዉ፡፡ጉዳቱ በደረሰበት ጊዜ ሲከፈላቸዉ በነበረዉ ደመወዝ ታስቦ እንዲከፈላቸዉ የተወሰነዉ በአዋጅ ቁር 1156/2011 አንቀጽ 189፣139/ሠ እና 165(1 እና 5) ስር የተደነገገዉን መሰረት ያደረገ ስለሆነ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም ሰበር አጣሪ ችሎት ከመሰረተዉ ጭብጥ በተጨማሪ ተጠሪ የአመልካችን የሥራ ዉል በሕጋዊ መንገድ ነዉ ያቋረጠዉ ተብሎ በመወሰኑ እና አመልካች እንዲከፈላቸዉ የጠየቋቸዉን ክፍያዎች በከፊልና በሙሉ ዉድቅ ተደርጎ በመወሰኑ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረቱት በሥራ ላይ እያለሁ በደረሰብኝ ቋሚ የአካል ጉዳት ምክንያት ተጠሪ በቀን 10/09/2011ዓ/ም ከሕግ-ዉጭ አሰናብቶኛል በማለት ነዉ፡፡ተጠሪ አመልካችን በቀን 10/09/2011ዓ/ም ማሰናበቱን ሳይክድ ተጠሪ የተሰናበቱት በአ.ኤ.አ በ2015 የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከተሰጣቸዉ በኋላ እ.ኤ.አ በ2016 እና 2017 በፈጸሙት ጥፋት መሰረት በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(1/ሐ እና መ) መሰረት ስለተሰናበቱ የሥራ ዉሉ በሕጋዊ መንገድ የተቋረጠ ነዉ በማለት ተከራክሯል። የወረዳዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ላይ እንደተመለከተዉ አመልካች ክሱ በተሰማበት እለት ተጠሪ በአዋጁ አንቀጽ 27/3 መሰረት በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ የስንብት እርምጃ ያልወሰደ በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል በማለት በቃል ተከራክረዋል።በቀድሞዉ አሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996ም ሆነ ይህንን አዋጅ በተካዉ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27/3 ስር አንድ አሠሪ በአዋጁ አንቀጽ 27/1 መሰረት የሥራ ዉሉን ለማቋረጥ ያለዉ መብት ዉሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መኖሩን ካወቀ ከሰላሳ የሥራ ቀናት በኋላ በይርጋ እንደሚታገድ ደንግጓል።በዚህ ድንጋጌ ላይ ተመስርቶ ሠራተኛዉ የሥራ ዉሉ የተቋረጠዉ የሰላሳ የሥራ ቀናት ካለፈ በኋላ ነዉ የሚል የይርጋ መከራከሪያ ሲያቀርብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 244/1 እና 245 ስር በተደነገገዉ መሰረት ጉዳዩን የሚዳኘዉ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አሠሪዉ የሥራ ዉሉን ያቋረጠዉ ሠራተኛዉን የሚያሰናብ ጥፋት መፈጸሙን ባወቀ በሰላሳ የሥራ ቀናት ጊዜ ዉስጥ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን መርምሮ አስቀድሞ ዉሳኔ መስጠት ይኖርበታል። በያዝነዉ ጉዳይ ላይ አመልካች ስንብቱ የተፈጸመዉ ጥፋት ተፈጸመ ከተበላ ከ30 ቀን በኋላ በመሆኑ በይርጋ የታገደ ነዉ የሚል ክርክር ያቀረቡ ቢሆንም የወረዳዉ ፍርድ ቤት በዚህ መከራከሪያ ላይ ግልጽ ዉሳኔ አልሰጠም፣በዚህ አግባብ በግልጽ በቀረበ ክርክር ላይ ዉሳኔ አለመስጠቱ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ጉድለት ነዉ። ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር ያዩ ፍርድ ቤቶችም በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበዉን ቅሬታ መሰረት አድርገዉ ተገቢዉን ዉሳኔ መስጠት ሲገባቸዉ በዝምታ ማለፋቸዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ።ስለሆነም በመጀመሪያ ተጠሪ የአመልካችን የሥራ ዉል ያቋረጠዉ በሕጉ የተመለከተዉ የይርጋ ጊዜ ሳያልፍ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ጭብጥ ተመርምሮ ሊወሰን ይገባል።ቀጥሎም የሥንብቱ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑ በስረ ነገሩ ተመርምሮ የሚደረስበት መደምደሚያ ላይ በመመስረት ከክፍያ አንጻር ሕጋዊ የሚኖረዉ ዉጤት ላይ ዉሳኔ ሊሰጥ ይገባል።

በሌላ በኩል ከወዲሁ ሊወሰኑ የሚችሉ ክፍያዎችን በተመለከተ እንደመረመርነዉ አመልካች ያልተጠቀሙት የ2 ዓመት የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተለዉጦ እንዲከፈላቸዉ ጠይቀዋል። ተጠሪ ደግሞ አመልካች ያልተጠቀሙት የአመት እረፍት የለም ብሎ ሳይክድ በሕጋዊ መንገድ ቅጽ ሞልተዉ ስላላስተላለፉ ሊከፈላቸዉ አይገባም በማለት ተከራክሯል።የስር ፍርድ ቤት አመልካች ያልተጠቀሙት የ51 ቀን የዓመት እረፍት እንዳላቸዉ ተጠሪ ቢያምንም አመልካች ሌላዉን አመልካች እንደተጠቀሙ በመግለጽ አመልካች እንዲተላለፍላቸዉ ጠይቀዉ ያስተላለፉት የ2011ዓ/ም ስለሆነ የሥራ ዉላቸዉ እስከተቋረጠበት ጊዜ ድረስ ያለዉን ከግምት በማስገባት ያላቸዉ የዓመት እረፍት የ32 ቀናት ነዉ በማለት ወደ ገንዘብ ተለዉጦ ብር 9047.46 እንዲከፈላቸዉ ወስኗል።የሥራ ዉሉ ተቋረጠ በተባለበት ጊዜ(በቀን 10/09/2011ዓ/ም ) በሥራ ላይ በነበረዉ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 79(2 ፣3 እና 5) መሰረት የዓመት ፈቃድ በሠራተኛዉ ጠያቂነትና በአሠሪዉ ፈቃድ እንዲሁም የሥራ ሁኔታ ሲያስገድድ በአሠሪዉ ዉሳኔ የዓመት እረፍት ለሚቀጥለዉ ሁለት ዓመት ሊራዘም ይችላል።አሠሪ ሠራተኛዉ በሥራ ላይ አልነበረም ወይም ደግሞ

የዓመት እረፍቱን ተጠቅሟል የሚል ክርክር ካላቀረበ የሥራ ሁኔታዉ በማስገደዱ በአሠሪዉ ዉሳኔ የዓመት እረፍት እንደተላለፈ ሊቆጠር ይገባል፡፡በያዝነዉ ጉዳይ አመልካች ማስተላለፍ የሚችሉት የሁለት አመት እረፍት ብቻ ሆኖ ከዚህ ላይ የአንድ አመት አመልካች መጠቀማቸዉ ስለተረጋገጠ ያልተጠቀሙት የዓመት እረፍት በአዋጁ አንቀጽ 77/5 መሰረት ወደ ገንዘብ ተለዉጦ እንዲከፈላቸዉ ስለተወሰነ በዚህ ረገድ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡

እንዲሁም ተጠሪ የአመልካችን የሥራ ዉል ሲያቋርጥ አመልካች ያልተጠቀሙትን የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ለዉጦ በአዋጁ አንቀጽ 36 መሰረት በሰባት የስራ ቀናት ዉስጥ ያልከፈለና ያልከፈለበትምን ሕጋዊ ምክንያት ያላስረዳ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ክፍያዉ ለዘገየበት በአዋጁ አንቀጽ 38 መሰረት ተጠሪ ቅጣት እንዲከፍል አለመወሰናቸዉም ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ላይ ለደረሰዉ ቃሚ የአካል ጉዳት ተጠሪ ካሳ እንዲከፍል ሲወሰን አመልካች ላይ ጉዳት በደረሰበት ጊዜ ለአመልካች ሲከፈላቸዉ የነበረዉን ደመወዝ መሰረት በማድረግ የወሰነዉን በተመለከተ አመልካች የአዋጁን አንቀጽ 109 የሚቃረን ነዉ በሚል የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ዉሳኔዉ ሕግን መሰረት ያደረገ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡በአዋጁ አንቀጽ 109 ላይ ካሳዉ የሚሰላዉ በሠራተኛዉ ላይ ጉዳት በደረሰ ጊዜ ሲከፈላቸዉ በነበረዉ ደመወዝ ነዉ ወይስ ለሠራተኛዉ ክፍያ በሚፈጸምበት ጊዜ ሲከፈል በነበረ ደመወዝ ነዉ የሚለዉን ሕጉ በግልጽ አልደነገገም፡፡የአመልካች የሥራ ዉል በተቋረጠበት ጊዜ የአመልካች ደመወዝ መጠን ብር 8482.00 እንደነበረ ተጠሪ ባይክድም በአመልካች ላይ ጉዳት በደረሰ ጊዜ ግን የአመልካች ደመወዝ ብር  4306.00 እንደነበር ተረጋግጧል፡፡አመልካች የጉዳት ካሳ ወዲያዉ ወይም እጅግ ቢዘገይ በአዋጁ አንቀጽ 162/3 ስር የተደነገገዉ የ6 ወር የይርጋ ጊዜ ከማምት ገብቶ ሲታይ አመልካች ይህ የ6 ወር ጊዜ ሳያልፍ ክፍያ ይጠይቃሉ ተብሎ ይገመታል፡፡በመሆኑም በዚህ ጊዜ ዉስጥ አመልካች ደመወዛቸዉ ከብር 4306.00 በላይ እንደሆነ ካለማስረዳታቸዉ በላይ ካሳ እንዲከፈላቸዉ ሳይጠይቁ በመቆየታቸዉ ምክንያት ረጅም ጊዜ ቆይቶ የደመወዝ ጭማሪ በመደረጉ ምክንያት አመልካች ጉዳቱ እንደደረሰ ወዲያዉ ካሳ ቢጠይቁ ኖሮ ሊከፈላቸዉ ከነበረዉ ደመወዝ በላይ በሆነ መጠን ካሳ ሊሰላ አይገባም፡፡ስለሆነም የአመልካች ደመወዝ በብር 4306.00 ታስቦ ካሳ እንዲከፈላቸዉ በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ ስህተት የለም ብለናል፡፡በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የአንፊሎ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 20357 ላይ በቀን 15/07/2012ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ ፣የቀለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 29410 ላይ በቀን 13/09/2012ዓ/ም የሰጠዉ ብይን እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 333150 ላይ በቀን 06/04/2013ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሻሽለዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

2. ተጠሪ የአመልካችን የሥራ ዉል በሕጋዊ መንገድ አቋርጧል ተብሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ ተሽሯል፡፡ አመልካች ላልተጠቀሙበት የዓመት እረፍት ብር 9047.46፣የፕሮቪደንት ፈንድ ብር 105,205.17 እና የጉዳት ካሳ ብር 51,672.00 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል የተሰጠዉ ዉሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡እንዲሁም ተጠሪ የአመልካችን የዓመት እረፍት ስንብቱን ሲፈጸም ወደ ገንዘብ ለዉጦ ባለመክፈሉና ክፍያ ስላዘገየ ቅጣት የሁለት ወር ደመወዝ ብር 16,964.00 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል ተወስኗል፡፡

3. የአንፊሎ ወረዳ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ ተጠሪ አመልካችን ለማሰናበት መሰረት ያደረገዉ ማሰናበቻ ምክንያት መኖሩን(መከሰቱት) ያወቀዉ ከመቼ ጀምሮ ነዉ የሚለዉን በመለየት የአመልካችን የሥራ ዉል የሚያስቋርጥ ምክንያት መኖሩን ከወቀበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ የሥራ ቀናት ዉስጥ የሥራ ዉሉን አቋርጧል ወይስ አላቋረጠም? የሚለዉን ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ አንጻር በማረጋገጥ የሚደርስበትን ድምዳሜ መሰረት በማድረግ ሕጋዊ ዉጤቱን እንዲወስን? እንዲሁም ተጠሪ የሥራ ዉሉን ያቋረጠዉ ሰላሳ የሥራ ቀናት ጊዜ ሳያልፍ ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ የሚደረስ ከሆነም የሥንብቱን ሕጋዊ መሆን አለመሆንና ሕጋዊ ዉጤቱን መርምሮ ተገቢዉን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1 መሰረት መልሰንለታል፡፡

4. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. በዉሳኔዉ መሰረት እንዲፈጽም የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም